# ኢ-ቢስክሌት እና ኢ-ስኩተር (e-bikes and e-scooters) ደህንነት

የኤሌትሪክ ብስክሌቶች እና የኤሌትሪክ ስኩተሮች (e-bikes and e-scooters) ተወዳጅነት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ጨምሯል። አብዛኛውን ጊዜ የሊቲየም-አዮን (Lithium-ion) ባትሪዎች ለሁሉቱም የኃይል ምንጭ ናቸው እና በትክክል ጥቅም ላይ ካልዋሉ ወይም ከተበላሹ ባትሪዎቹ በእሳት ሊያያዙ ወይም ሊፈነዱ ይችላሉ። ኢ-ቢስክሌቶችን ወይም ኢ-ስኩተሮችን እንደ ዋና የመንቀሳቀሻ መንገድ ወይም ለመዝናናት የሚጠቀሙባቸው ከሆነ እነዚህን መሳሪያዎች ቻርጅ ሲያደርጉ ወይም ሲያስቀምጡ ልብ ሊሏቸው የሚገቡ ጠቃሚ የደህንነት ምክሮች አሉ።

## ችግሩ

- የተበላሹ ወይም የማይሰሩ ባትሪዎች ሊሞቁ፣ ሊያቃጥሉ ወይም ሊፈነዱ ይችላሉ።
- የሊቲየም-አዮን የባትሪ እሳቶች መርዛማ ጋዞችን ይለቃሉ እና በጣም ይቀጣጠላሉ።

## የደህንነት ምክሮች

- በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚታወቅ የሙከራ ላብራቶሪ በኩል የተዘረዘሩ እና በዚሁ መሰረት መግለጫ የተለጠፈባቸውን መሳሪያዎችን፣ ባትሪዎችን እና ቻርጅ ማድረጊያዎችን ብቻ ይግዙ እና ይጠቀሙ።
- ሁልጊዜ የአምራቹን መመሪያ ይከተሉ።
- ለመሳሪያው እንዲሆኑ ተብሎ የተሰራ እና ከእቃው ጋር አብሮ የመጣውን ባትሪ እና ቻርጅ ማድረጊያ ብቻ ይጠቀሙ።
- ሙሉ በሙሉ ቻርጅ ከተደረገ በኋላ መሳሪያውን ወይም የመሳሪያውን ባትሪ ቻርች ማድረግ ያቁሙ።
- ሰርኪውቱ (circuit) ላይ ከመጠን በላይ ጫና እንዳይፈጠር ለመከላከል በአንድ ጊዜ አንድ መሳሪያ ወይም የመሳሪያ ባትሪ ብቻ ቻርጅ ያድርጉ።
- በተቻለ መጠን ባትሪዎችን በመካከለኛ የሙቀት መጠን ባለው ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ። ከ32°F (0°C) በታች ወይም ከ105°F (40°C) በላይ በሆነ የሙቀት መጠን ቻርጅ አያድርጉ።
- ባትሪዎችን ቀጥታ የፀሀይ ብርሀን በሚያገኙበት ስፍራ ወይም በሞቃት ተሽከርካሪዎች ውስጥ አያስቀምጡ እና ከልጆች እና ፈሳሽ ከሆኑ ነገሮች አርቀው ያስቀምጡ።.
- ኢ-ብስክሌቶችን፣ ኢ-ስኩተሮችን እና ባትሪዎችን ከመውጫ በሮች ሊሞቁ ወይም ሊቃጠሉ ከሚችሉ ነገሮች አርቀው ያስቀምጡ።
- መሳሪያዎች ለማስጠገን ብቃት ባለው ባለሙያ ብቻ ያሠሩ።
- የሊቲየም-አዮን ባትሪዎችን በቆሻሻ መጣያ ውስጥ አይጣሉ። እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ሁልጊዜ ጥሩው አማራጭ ነው። ባትሪዎቹን ወደ ባትሪ እንደገና ጥቅም ላይ የሚያውል ቦታ ይውሰዱ ወይም የማስወገጃ መመሪያዎችን ለማግኘት የአካባቢዎን የቆሻሻ ማስወገጃ ዲፓርትመንትን ያነጋግሩ።

## ችግር መኖሩን የሚያሳዩ ምልክቶች

በባትሪው ላይ ከእነዚህ ችግሮች ውስጥ አንዱን ካስተዋሉ ኢ-ብስክሌት ወይም ኢ-ስኩተር መጠቀም ያቁሙ፣ ያልተለመደ ሽታ፣ ቀለም መቀየር፣ ከመጠን በላይ ሙቀት፣ የቅርጽ ለውጥ፣ ፈሳሽ ማታየት፣ ጭስ ወይም ቻርጅ አለማድረግ።.

## እሳት ካዩ...

ወዲያውኑ ሕንፃውን ለቀው ይውጡ፣ እሳቱን ለማጥፋት እንዳይሞክሩ ነገር ግን ወደ 911 ይደውሉ።

ለነጻ የቤት ደህንነት ፍተሻ ወደ 311 ይደውሉ፣ www.mcfrs.org/mcsafe